የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፭ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 7
ADDIS ABABA December 15th 2011


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፪፻፶፯/፪ሺ፬

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..................... ገጽ ፮ሺ፪፻፶፪


**CONTENTS**


Regulation No. 257/2011

Science and Technology Information Center Establishment Council of Ministers Regulation .................................................................................. Page 6252


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፯/፪ሺ፬

## የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና አንቀፅ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፯/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ" ማለት ቴክኖሎጂዎችን፣ የምርምር ውጤቶችንና የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት በጽሁፍ ወይም በኦዲዮቪዥዋል ወይም በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ተጠናቅሮ የሚገኝ መረጃ ነው፤

፪/ "ቴክኖሎጂ" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በጽንሰ ሃሳብ፣ በመሣሪያና በአመራረት ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት የተከማቸ ዕውቀት ነው፤

፫/ "የቴክኖሎጂ ሽግግር" ማለት ለምርትና ለአገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን ከሚገኙበት ቦታ ወደ ኢኮኖሚው ማስገባትና በተሟላ ሁኔታ በመረዳት ለመጠቀም፣ ለመጠገን፣ ለማሻሻልና ብሎም በሀገር ውስጥ ለመሥራት መቻል ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 257/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF SCIENCE AND TECHNOLOGY INFORMATION CENTER

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Science and Technology Information Center Establishment Council of Ministers Regulation No. 257/2011".

2. ***Definitions***

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "science and technology information" means information about technologies, research outputs and scientific and technological activities that is found in written or audiovisual or various other electronic forms;

2/ "technology" means knowledge that enables production of goods and services and that is embodied in concepts, equipment and production or service process;

3/ "technology transfer" means acquiring technologies from where they are available and introducing them into the production process, and creating the capability to properly understand, use, repair, adapt and ultimately develop them locally;

፬/ "የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋም" ማለት የመንግሥት የምርምር ተቋም፣ ዩኒቨርሲቲ፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ ተቋም ሆኖ በጥቃቅን፣ በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂ ከውጭ የማስገባትና የማሸጋገር ሥራ ለመደገፍ የሚሠራ አካል ነው፡

፭/ "ሳይንስ" ማለት ተፈጥሯዊ አካላትን፣ ሂደቶችንና ክስተቶችን ለመረዳት ከሚደረግ ምርምር የሚገኝ ዕውቀትና ይህንን ዕውቀት ለማመንጨት ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው፤

፮/ "ምርምር" ማለት አዲስ ዕውቀትን ለማመንጨትና ጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ነባር ዕውቀትን ጥቅም ላይ ለማዋል ሥርዓት ባለው መንገድ የሚከናወን ተግባር ነው፤

፯/ "ኢኖቬሽን" ማለት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ ግንኙነቶችን ወይም የመገበያያ ዘዴዎችን በተቀናጀ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፤

፰/ "ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. መቋቋም

፩/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል (ከዚህ በኋላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቋሟል፡፡

፪/ ማዕከሉ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡

፭. የማዕከሉ ዓላማ

የማዕከሉ ዓላማ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለምርምርና ለማምረቻ ተቋማት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን በማፈላለግ፣ በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በማሰራጨት የሀገሪቱን ልማት ማፋጠን ይሆናል፡፡

፮. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

የማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ዘዴዎችንና መርሀ-ግብሮችን ማዘጋጀትና መረጃዎችን ማሰባሰብ፤

4/ "technology transfer institute" means a public research institute, a university, an institute of technology, a technical and vocational education and training center or any other organization that is engaged in supporting the technology transfer and introduction activities of micro, small, medium and large enterprises;

5/ "science" means the knowledge acquired from research undertaken to understand natural objects, processes and phenomena and the method of acquiring this knowledge ;

6/ "research" means any systematic activity undertaken to generate and apply new knowledge or to discover new applications of the existing knowledge;

7/ "innovation" means an integrated activity to use and apply new technologies, relations and marketing mechanisms;

8/ "Ministry" means the Ministry of Science and Technology;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. ***Establishment***

1/ The Science and Technology Information Center (hereinafter the "Center") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Center shall be accountable to the Ministry.

4. ***Head Office***

The Center shall have its head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. ***Objective of the Center***

The Center shall have the objective to accelerate the development of the country through searching, collecting, organizing, analyzing and disseminating information required for technology transfer, research and input for production entities.

6. ***Powers and Duties of the Center***

The Center shall have the powers and duties to:

1/ design mechanisms and programs to collect and make use of science and technology information and collect the information accordingly;

፪/ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በመተንተን እሴት አክሎ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፤

፫/ ከሀገር ልማት አንፃር ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የቴክኖሎጂ መረጃዎች በመምረጥ ረገድ ተጠቃሚዎችን መደገፍ፤

፬/ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሲገቡ ዝርዝር መረጃዎችን በመያዝ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂ የት እንደሚገኝ የተሟላ የመረጃ ቋት መያዝ፤

፭/ የሀገሪቱን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አመላካቾች በመለየት የአመላካቾቹን የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት መዘርጋት፤ መረጃዎቹን በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግና ተንትኖ ማሳተም፤

፮/ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በሚመለከት የተጠቃሚዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዳ መልዕክት የሚያስተላልፉ ጽሑፎችን ያካተቱ መጽሔቶችን፣ ሌሎች ጽሑፎችንና የማስተዋወቂያ ቁሶችን እያዘጋጀ ማሰራጨት፤

፯/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ከማደራጀት፣ ከመተንተንና ከማሰራጨት ጋር የተያያዙ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ አማራጭ ሀሳቦችን ማቅረብ፤

፰/ የሀገሪቱን የሣይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ሥርዓት በማዕከላዊነት መምራትና ማስተባበር፤

፱/ ከቴክኖሎጂ መረጃ ትንተና አቅም አንፃር የሚታየውን ፈጣን ዕድገት በመከታተል ለምርምርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ድጋፍና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፤

፲/ ሪፖርቶችን፣ መጽሔቶችንና መጻህፍትን የመሳሰሉ ወቅታዊ የሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ጽሑፎችን በማሰባሰብ ለተመራማሪዎች፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለማምረቻ ተቋማት ማሰራጨትና የቤተመፃሕፍት አገልግሎት መስጠት፤

፲፩/ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ትብብር መመሥረትና ጠቃሚ ልምዶችን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችንና አሠራሮችን ቀምሮ ወደ ሀገራችን ውስጥ ማስገባትና መተግበር፤

፲፪/ ጠንካራ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የመረጃ ኔትዎርክ መዘርጋት፤ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ተቋማት እንዲቋቋሙ መደገፍና የመረጃ ኔትዎርኩን አቅም በየጊዜው እያሳደገ መሄድ፤

፲፫/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ተመጣጣኝ ክፍያ መጠየቅ፤

፲፬/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፲፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

2/ make available value added technology information to users;

3/ support users in selecting technological information that has strategic importance from the national development perspective;

4/ maintain a complete database on the type and location of technologies through codification of detailed information on new imported technologies;

5/ identify national science, technology and innovation indicators and establish a system to collect information on these indicators; and periodically update, analyze and publish the information thereof;

6/ produce and disseminate bulletins, other publications and popularization materials that contain messages to raise the awareness of users regarding the value of technology information;

7/ carry out research and forward alternative ideas related to organization, analysis and dissemination of science and technology information;

8/ guide and coordinate the national science and technology information system as its principal organ;

9/ support the activities of research and technology transfer institutes and provide them with up-to-date information by tracking the advancement of technological information analysis capability;

10/ collect and disseminate up-to-date research literature such as reports, journals and books and render library services to innovators, researchers, industries and higher education institutions;

11/ establish cooperation with similar local and foreign institutes and bring in and apply best practices of their relevant experiences;

12/ establish strong local and international information network; support establishment of organizations with similar objectives and augment the capability of the network;

13/ collect, as appropriate, reasonable fees for services it renders;

14/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

15/ perform such other related activities that assist the attainment of its objectives.

**፯. የማዕከሉ አቋም**

ማዕከሉ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

**፰. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የማዕከሉን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የማዕከሉን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የማዕከሉን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ማዕከሉን ይወክላል፤

ረ) የማዕከሉን የስራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለማዕከሉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለማዕከሉ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፱. በጀት**

የማዕከሉ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲. የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**7. *Organization of the Center***

The Center shall have:

1/ a Director General and, as necessary, a Deputy Director General to be appointed by the government; and

2/ the necessary staff.

**8. *Powers and Duties of the Director General***

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Center and shall direct and administer the activities of the Center.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Center specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Center in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees engaged in the core functions of the Center, in accordance with directive approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work program and budget of the Center and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Center;

e) represent the Center in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry performance and financial reports of the Center.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Center to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Center.

**9. *Budget of the Center***

The budget of the Center shall be allocated by the government.

**10. *Books of Accounts***

1/ The Center shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Center shall be audited annually by the Auditor General or auditors assigned by him.

**፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፭ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**11. *Effective Date***

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 15th day of December, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**